# ሌላው ምሥራች!

## ለኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች!

## + + +

## ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ፡ ከኢትዮጵያዊው ሰውነትና ከኢትዮጵያ ምድር እየተባረረ ነው!

## + + +

### መቅድም

በኀዋ ሰሌዳችንና በመጽሓፎቻችን አማካይነት፡ እስካኹን በተላለፉት የእግዚአብሔር መልእክቶች እንዳመለከትነው፡ በሺህኛው ዓመተ ምሕረት ማብቂያና በ፪ሺህኛው መባቻ ላይ፡ ለጥቂት ጊዜ የተፈታው፡ ርኩስ መንፈስ፡ መሰሎቹና አጫፋሪዎቹ ከኾኑት የሰው ልጆች ጋር በመተባበር፥ በእነርሱዉም መሣሪያነት በመጠቀም፡ የክፋት ድርጊቱን፡ እንደማንኛውም፡ ሲኾን እንደኖረው ነገር ኹሉ፡ አኹንም፡ ባለው የመጨረሻ ኃይል፡ በዓለም ላይ የፈለገውን ሊፈጽም እንዲቻለው፥ ይህም፡ በእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ ታውቆ የሚካኼድ መኾኑ፡ በራእየ ዮሓንስ ተነግሮ ከተጻፈው የመንፈስ ቅዱስ ቃል ይነበባል።

ይህም የኾነው፡ ያለበቂ ምክንያት አይደለም፤ በምድር ላይ እየበዙና እየሠለጠኑ፥ እየተደራጁም የኼዱት የሰው ልጆች፡ በራሱ መልክ በመፍጠር፡ ፍጹሙን እውቀትና ነጻነት፥ ሀብትና በረከት፥ ሥልጣንና ኃይል ያስገኘላቸውን፥ ከዚህ የተነሣም፡ ዘለዓለማዊዉን የልዕልናና የክብር ዘውድን ያቀዳጃቸውን፡ የፈጠራቸውን እግዚአብሔርን፡ በገሃድ ክደው፥ በእርሱም ላይ ዓምፀው፡ የአምልኮ ምንዝርናን፡ ያለገደብ መፈጸማቸውን በመቀጠላቸው፥ ይኸውም፡ ለመልካም ሕይወታቸው መመሪያ እንዲኾናቸው የሰጣቸውን ሥርዓት ንቀውና አቃልለው በመተዋቸው፥ ከእርሱም ጋር፡ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው፡ በፈቃዳቸውና በፍላጎታቸው የተጋቡትን ቃል ኪዳን፡ በድፍረትና በማናለብኝነት በማፍረሳቸው መኾኑን፡ ባለራእዩ፡ እዚያው በመልእክቱ፡ አረጋግጦ ገልጾታል።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ በመጨረሻው ዘመን "ይደርሳሉ!" ተብለው የተነገሩት ምልክቶች ኹሉ፡ በሙሉ እውን ኾነው እየተካኼዱና እየተፈጸሙ በሚታዩበት፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ይህን የመሰለው፡ "የሰው ልጆች" ክህደትና ዓመፅ፣ እንዲሁም፡ የአምልኮ ምንዝርናና ልዩ ልዩ ኃጢአት፡ ከሚያደርሰው መከራና ሥቃይ፥ እልቂትና ጥፋት፡ ተከልለውና ተጠብቀው የሚገኙ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" መኖራቸውን፡ ባለራእዩ፡ እዚያው፡ በምሥራች መልእክቱ ውስጥ አሥፍሮታል። እነዚያም፡ መለኮታዊዉንና ረቂቁን፡ የቃል ኪዳን ማኅተም በያዘው በየራሳቸው ሰውነትና ማንነት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር ሕዝብነቷን፥ የእግዚአብሔር አገርነቷንና የእግዚአብሔር መንግሥትነቷን ጠብቃ፡ የነጻነት ህልውናዋን የቀጠለች መኾኗን፡ በእምነታቸው ምግባርና በሕይወታቸው አካኼድ አረጋግጠው ያሳዩትና እያሳዩ ያሉት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ናቸው።

ከዚህ የተነሣ፡ እንኳንስ፡ ግዙፉ፡ የሰው ልጆች፡ የጠላትነት ጥቃት ይቅርና፡ ረቂቁ የክፋት መንፈሳውያን ኃይላት ተፃራሪነትም እንኳ ቢኾን፡ ሊነካቸው ሳይችል ኖርዋል፤ ይኖራልም። በዚህ ረገድ፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ የሚደርስባቸው ፈተናና መከራ እንኳ ቢኖር፡ ኹሉንም በድል አድራጊነት ስለሚያሳልፉትና ስለሚያልፉት፡ ጥቃቱን፡ እንደጥቃት እንኳ አይቆጥሩትምና ነው።

<u>የመልእክቱ ቍም-ነገር</u>

እስኪ አኹን፡ ለዚህ መልእክት መነሻና መንደርደሪያ፥ መድረሻም ወደኾነን ቍም ነገር በቀጥታ እንኺድና፡ ያን የምሥራች እውነታ በጥሞና እንመርምር! እርሱም፡ ርኩሳን መናፍስት፡ በተለያየ መንገድና ሰበብ፡ በሰዎች ሰውነት ውስጥ እያደሩ፡ በሥጋዊው፥ በነፍሳዊውና በመንፈሳዊው ጤናማ ሕይወት ላይ የሚያስከትሉትን ጠንቀኛ ቀውስ የሚመለከተው ነው። ደግሞም፡ በዚህ አንጻር፡ ይህን የመሰለው ጠንቀኛ ቀውስ፡ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት፡ በታማኝነት አጽንተው በያዙ፥ በምግባራቸውም፡ እውን አድርገውት በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ እንዴት ሊታይ እንዳልቻለ፥ ምናልባት ግን፡ ከአንዳንዶች፡ የእምነት ጒድለትና የምግባር ስንኵልነት የተነሣ፡ የደረሰ ችግር ቢኖር እንኳ፡ ከእነዚያ ግለሰቦች፡ እንዴት ሊወገድ እንደቻለ የሚያስረዳው ነው።

አዎን! የክፋትና የሓሰት አባት በተባለው፡ በዲያብሎስ የበላይ መሪነት፡ "ሰይጣናት"፥ ወይም፡ "አጋንንት"፥ ወይም፡ "ዛር ውላጅ"፥ ወይም፡ "ልቡሳነ-ሥጋ" ማለትም፡ "ፍጥረታዊዉን ግዙፍ ሥጋ የለበሱ" በሚል፡ በሌላ፡ የተለያየ ስም ሳይቀር የሚታወቁት ርኩሳን መናፍስት፡ በግል ምርጫና ውሳኔ፥ ወይም፡ በዘር ሓረግ ግዳጅ፡ በባዕድ አምልኮ ልማድ፡ በግል ሰውነት ውስጥ ገብተው እያደሩና በትውልድ፡ ከወላጅ ወደልጅ እየተላለፉ፡ በግለሰቦችና በቤተሰብ፥ በኅብረተሰብና በአገረሰብ ደረጃ፡ ፍጥረተ ዓለሙን ሲጠናወቱትና ሲቆራኙት፥ ሲያምሱትና ሲያሠቃዩት፥ ሲያፋጁትና ደም በደም እያፋሰሱ ሲያተላልቁት መኖራቸው፥ በታሪክ ብቻ ሳይኾን፡ በዛሬውም ኹኔታ ይኸው ጎልቶ የሚታወቅ ግልጽ እውነታ ነው።

ይኹን እንጂ፡ እጅግ በርካታ ከኾኑት መካከል፡ ጥቂቶቹን ለመምረጥ ያህል፡ በኖኅ ዘመን ለደረሰው የጥፋት ውኃና በነአብርሃም ጊዜ ግብረ ሰዶማውያንን ለደመሰሰው ገሞራዊ እሳት፥ በቅርቡም፡ በ፳ኛው ምዕት ዓመት፡ ብዙዎችን ለእልቂት ለዳረገው፡ ለ፪ኛው የዓለም ጦርነት፡ ምክንያቱ፡ ራሱ፡ የሰዎች ክፉ ምርጫ መኾኑ ቢታወቅም፡ የርኩሳን መናፍስትም ግዙፍ አስተዋጽኦና ጽኑ ተባባሪነት መኖሩ እርግጥ ነው። እዚህ ላይ፡ ልንጠቅሰውና ልናተኩርበት የምንሻው ግን፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በቀላሉ ሊያስወግደው የሚቻለውን ወገን ይኾናል።

በሰዎች ዘንድ፡ ከዓቅማቸው በላይ በኾኑ ምክንያቶች መነሻነት ከሚደርሰው ይልቅ፡ እጅግ ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ፥ የከፋና የሚጎዳም ኾኖ የሚገኘው፡ በየራሳቸው ፍላጎትና ምርጫ የሚያመጡት ችግር መኾኑ፡ ከታወቀ ቆይቷል፤ ለዚህም ብሂል ትክክለኛነት፡ የመጀመሪያዎቹን ሰዎች፡ የአዳምንና ሔዋንን ዝክረ ነገር ያስታውሷል። ይህም ማለት፡ ርኩሳን መናፍስት፡ በሥጋዊው፥ በነፍሳዊውና በመንፈሳዊው የሰዎች ጤናማ ህልውና ላይ የሚኖራቸውን፡ ጠንቀኛ ተፅዕኖ ተቋቁመው፡ እየራሳቸውን ከሕመም ነጻ ለማድረግ፡ የየግለሰቦች የሃይማኖት እውነተኛነትና ጽናት፥ የየምግባራቸው ትክክለኛነትና ጥንካሬም ወሳኝ መኾኑ፡ በእርግጠኛነት ሊታመንበት ይገባል ማለት ነው።

በዚህ ረገድ፡ አንድ ሰው፥ (እርሱም፡ ኢትዮጵያዊው)፡ በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት፡ እውነተኛና ፍጹም ከኾነ፥ በእርሱ የሚያድርበት መንፈስ ቅዱስ መኾኑ፡ ሊጠረጠር አይቻልም፤ አይገባምም። ከዚህ እውነታ የተነሣ፡ ርኩስ መንፈስ፡ ለፈተና የተላከውም ቢኾን፡ በዚያ ሰብአዊ ቤተ መቅደስ ውስጥ፡ እንኳንስ ሊገባ ይቅርና፡ ወደእርሱ ሊቀርብ፥ በአጠገቡ ሊያልፍና አሻግሮ ሊመለከት እንኳ አይደፍርም። የዚያ ሰው፡ እምነቱና እምነቱ ያስገኘው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ነደ እሳት ኾኖ፡ ገና ከሩቁ ያቃጥለዋልና።

ነገር ግን፡ ያ ሰው፡ በአስተሳሰቡና በንግግሩ፥ በአድራጎቱም፡ ከክፋት ጋር የወገነ ከኾነ፡ ለርኩሳን መናፍስት ማደሪያነት በቀላሉ የተመቸ ይኾንና የእነርሱ መጨፈሪያና የፍላጎታቸው ማካኼጃ ኾኖ፡ የኹለንተና ጤንነቱን በማጣት፡ በሕመም ጎሬነቱ የሥቃይ ኑሮውን ይቀጥላል።

ከዚህ በላይ ለተሠነዘረው አስተያየት፡ እጅግ ብዙዎች ከኾኑት የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት መካከል፡ "'***ይህ፡ በብዔል ዜቡል፡ በአጋንንት አለቃ ካልኾነ በቀር፡ አጋንንትን አያወጣም!'*** ላሉት የአይሁድ ፈሪሳውያን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ 'እኔስ፡ በብዔል ዜቡል፡ አጋንንትን የማወጣ ከኾንሁ፡ ልጆቻችሁ በማን ያወጧቸዋል? ስለዚህ፡ እነርሱ፡ ፈራጆች ይኾኑባችኋል። እኔ ግን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ፡ አጋንንትን የማወጣ ከኾንሁ፡ እንግዴህ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ወደእናንተ ደርሳለች!'" ሲል የሰጠውን መልስ፡ ለአብነት ያህል፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ ይበቃል። እነዚህንም፡የመሰሉት የምሥራች ዜናዎች፡ በአራቱ ባለብሥራቶችና በሌሎቹ ውስጥ የሚገኙት ናቸው። (ማቴ. ፲፪፥ ፳፪-፴፪ እና ሉቃ. ፰፥ ፳፯-፴፱።)

በዚህ ረገድ፡ በእነዚህ ቃላት መሠረት፡ ከአዳምና ሔዋን ጊዜ ጀምሮ እስከምንገኝበት፡ እስካኹኑ ዘመን ድረስ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ሲደረጉላቸው የኖሩትን መለኮታውያን የሕይወት ተአምራት ዝርዝር ዘገባ፡ ለሕያዉ የዜና መዋዕላችን ትተን፡ ከቅርብ ወራት ወዲህ ከደረሱት የምሥራች ዝክረ ነገሮች መካከል፡ ለዓይነት፡ ኹለት ያህሉን ብቻ፡ ቀጥለን እናቀርባለን።

፩ኛ. ወላጆቿ፡ ለትምህርት ወደአሜሪካን አገር ልከዋት፡ የተላከችበትንና የመጣችበትን ዓላማ በማካኼድ ላይ የነበረች አንዲት የከፍተኛ ደረጃ ተማሪ፡ ጽኑ የመንፈስ ጭንቀትና መታወክ ሕመም ስላደረባት፤ ከዚሁ ችግሩዋ ለመዳን፡ ጥረቷን፡ በራሷ በኩል ማድረግ ጀመረች፤ ያ ጥረቷ፡ አለመሳካቱ ገሃድ ሲኾን፡ ዐብራቸው ትኖር በነበሩት ዘመዶቿ በኩል በተደረገባት የግዳጅ ተፅዕኖ፡ ወደዘመናዊው ሥጋዊ ምክርና ሕክምና እንድታመራ ተገደደች፤ በዓለማውያንና ሥጋውያን ሰዎች ዘንድ፡ ሙሉ እምነት ተጥሎበት የነበረው፡ ያም ዘዴ፡ ኹኔታዋን እያባባሰው ከመኼዱ በቀር፡ ምንም ዓይነት የመሻሻል ፍንጭን ስላላሳየ፡ ልጂቱ፡ ፍጹም ተስፋ ወደመቁረጡ ቅጽበት ተቃረበች።

በዚህች አፍታ ነበር፡ "አምላከ ነዳያን፥ ወተስፋ ቅቡፃን!" ማለትም፡ "የደሆችና ተስፋ የቆረጡ አምላክ!" የሚባለውን እግዚአብሔርን፡ በፍጹም ልቦናዋና በእውነት መንፈስ ኾና የፈለገችው። በዚች ቀውጢ ሰዓት ነበር፡ ገና፡ በአገርዋ ሣለችና እንዲያውም፡ ከሕፃንነትዋ ጀምራ፡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች፡ ቀደም አድርጋ ታውቃቸው የነበሩትን፥ መጽሓፋዊ መልእክቶቻቸውንም፡ በመጠኑም ቢኾን ያነበበቻቸውን፡ የእግዚአብሔርዋ መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ የኾኑትን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ፡ ከቀደመ ምክራቸውና ትምህርታቸው፥ ማሳሰቢያቸውና ማስጠንቀቂያቸው ጋር፡ ከትዝታዋ ማኅደር ውስጥ አውጥታ ልታስታውሳቸው የቻለችው። በዚያ፡ የሥቃይዋና የጉሥቍልናዋ ጊዜ፡ ይህን የመሰለውን ትዝታ፡ ወደአእምሮዋ አምጥቶ የገለጠላት፡ መንፈስ ቅዱስ ሲኾን፥ ያን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ወደእርሷ ጠርቶ፡ ከዚያ እውቀትና በፈጣሪዋ ላይ ካላት መታመን የተነሣ፡ ለእውነተኛ ንስሓ እንድትበቃ ያደረጋት ደግሞ፡ የራሷ ውሳጣዊና ልባዊ እምነት መኾኑ፡ ሊጠረጠር ከቶ አይቻልም።

ከዚህ ብቅዓት ያደረሳት፡ የዚያ እምነቷ ተአምራዊ ኃይል፡ በዚህ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ረክቶና ተወስኖ አልቀረም፤ በሥቃይና በረሃብ በደከመ ጎኗ፡ ለእኚሁ ኢትዮጵያዊ ካህን ስልክ ደውላ ታነጋግራቸው ዘንድ አነሣሣት፤ አበረታታት፤ ጥንካሬውንም ሰጣት፤ ወዲያው፡ የካህኑን ስልክ ፈልጋና አስፈልጋ አስደወለች።

ካህኑ፡ ስልኩን አንሥተው፡ "እነሆ አለሁ!" አሉ።

ስልክ ደዋዩ፡ "እባክዎ! ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ አሉ?" አሉ።

"እኔ ነኝ!"

"እንግዲያ፡ እባክዎ! እኅተ ሚካኤል ልታነጋግርዎ ትፈልጋለች?"

"እሺ! ደስ ይለኛል።"

ከሕመሟ የተነሣ፡ አንዳችም እህል ውኃ ሳትቀምስ አድራ በመዋሏና በማምሸቷ፡ በሥቃይና በድካም ዝላ ያልወደቀችው ሕመምተኛዋ ወጣት፡ የተለመደ የሰላምታ ቃሎችን ካሰማች በኋላ፡ "እባክዎ ይድረሱልኝ? ጭንቀቴንና ሥቃዩን አልቻልሁትም፤ ቤተሰቦቼም፡ ያለእምነቴና ያለፈቃዴ፡ ይኸው እያስገደዱኝ፡ በሕክምናው ሊገድሉኝ ነውና፡ በቶሎ እንዲመጡልኝ እፈልጋለሁ!" አለች፡ በሰለለ የኀዘኔታ ድምፅ፥ ነገር ግን፡ በድፍረትና በቁርጥ ቃል።

ኢትዮጵያዊው ካህን፡ የሕመሟን ዓይነትና ኹኔታ፡ ከአንደበቷ እንደተረዱ፡ እንዲህ ሲሉ ንግግራቸውን ቀጠሉ፡- "አንቺ ከዚህ ከሚያሠቃይሽ ሕመም ለመዳን፡ በእውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችንና ምግባራችን መሠረት፡ የእኔ ወደአንቺ መምጣት፥ የአንቺም፡ ወደእኔ መምጣት አያስፈልግም።" ብለው ገና መልስ መስጠት ሲጀምሩ፡ ሕመምተኛዋ፡ አቋረጠቻቸው።

"እንዴት አያስፈልግም!"

"አዎን! አያስፈልግም። ምክንያቱን ልግለጥልሽ! በማስተዋል አዳምጪኝ!"

"እሺ!"

ኢትዮጵያዊው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡ ምክንያታቸውን መናገር ጀመሩ፡- "አንቺ እምነቱ አለሽ፤ የደወልሺልኝም፡ እምነቱ ስላለሽ ነው፤ ትልቁና ቀዳሚው ቍም ነገር ደግሞ፡ ይኼ ነው። የመጨረሻውን የመፍትሔ ኃይል፥ እርሱም፡ ፍቱኑን መድኃኒት ይዘሻል ማለት ነው፤ ለመፈወስሽ እርግጠኛነት፡ ምንም ጥርጣሬ አይኖርም። የሚያድንሽን፡ እምነትሽን፡ በመዳፍሽ ውስጥ ይዘሽው ትገኚያለሽ። የሚያድንሽ፥ እውነተኛውንም ፈውስ የሚሰጥሽ፡ እርሱ፡ የራስሽ እምነት እንጂ፡ እኔ አይደለሁም።

"'እምነትሽ! እምነትሽ!' የምለው፡ ይህ ሃይማኖትሽ፡ 'እውነተኛውና የሰባት ሺ አምስት መቶ ኹለት ዓመታት ዕድሜ ያለው፡ ኢትዮጵያዊው፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትሽን' ማለቴ መኾኑን ልትገነዘቢው እወድዳለሁ።"

ንግግራቸውንም እንዲህ ሲሉ ቀጠሉ፡- "ታውቂ የለምን? እንኳንስ እኔ ደካማውና ኃጢአተኛው ልቅርና፡ ራሱ ባለቤቱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሕመምተኞችን፡ ራሱ፡ በቃሉ፡ ማዳን ሲችል፡ ለምን ይመስልሻል፡ ወንዶቹን፡ ከተፈወሱ በኋላ፡ 'እምነትህ አዳነህ!' ሴቶቹንም፡ 'እምነትሽ አዳነሽ!' ይላቸው የነበረው? መዳን የሚቻለው፡ በራስ እምነት በመኾኑ ነው። ትክክለኛውና እውነተኛው እምነት ካለሽ፡ አዎን! በእርግጥ ትድኛለሽ። በእርግጥ ልትድኚ ከፈለግሽም፡ አስቀድመሽ ልታውቂውና ልትገነዘቢው የሚገባሽ ዋና ጉዳይ አለ።

"እርሱም፡ «በመጀመሪያ፡ በፈጣሪሽ ላይ ያለሽ እምነት፡ ትክክለኛና እውነተኛ መኾን አለበት፤ ቀጥሎ፡ 'ይህን እምነቴን፡ በምግባር የምፈጽመው ከኾንሁ፡ በእርግጥ እድናለሁ!' የሚል ቆራጥ ውሳኔን በውስጥሽ የሰጠሽ ኾነሽ መገኘት አለብሽ!' የሚለው እውነታ ነው። እነዚህ የሃይማኖትና የምግባር ኹለት ቍም ነገሮች፡ በአንቺ ዘንድ እንዲገኙ ካደረግሽ፥ በውስጥሽ የሚገኙ መኾናቸውንም፡ ለራስሽ ከተማመንሽ፡ ፈውስሽ የተረጋገጠ ይኾናል።"

ካህኑ፡ የምክንያታቸውን ማብራሪያ ማብቃታቸውን፡ በዝምታ ቆይታቸው እንደተረዳች፡ ሕመምተኛዋ፡ በነቃ ድምፅ፡ "አዎን! ፈጣሪዬ ሊያድነኝ እንደሚቻለው አምናለሁ፤ ዕድሉን ላግኝ እንጂ፡ ይህንኑም እምነቴን በተግባር ላይ ዐውዬ፡ ለእርስዎም፥ ለሌሎችም፡ ላሳይ እችላለሁ! ደግሞስ፡ ስልክ እንዲደወልልዎና እንዳነጋግርዎ የፈለግሁት፡ እምነቱ ቢኖረኝ አይደለምን? ለነገሩ ግን፡ እኔ፡ 'እምነቴ ነው!' የምለውና እርስዎ፡ 'እምነትሽ ነው!" የሚሉት እምነት፥ ወይም፡ ሃይማኖት፡ ምን ዓይነት እንደኾነ ለይቼ ለማወቅ፡ ቅድም፡ 'እውነተኛውና የሰባት ሺ አምስት መቶ ኹለት ዓመታት ዕድሜ አለው!' ስላሉት፡ ስለዚያ፡ 'ኢትዮጵያዊ፡ የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖት' እስኪ ያብራሩልኝ?!" በሚል መጠይቃዊ ቃል፡ ለካህኑ መልስ ሰጠች፤ የራስዋና ኢትዮጵያዊው ካህን የሚሉት እምነት፡ አንድ መኾኑን ብታውቀውም፡ እንደገና በይበልጥ ለማረጋገጥ ፈልጋ።

እርሳቸውም፡ በዚህ ምላሿ ተደስተው፡ "እውነትሽን ነው፤ መልካም ተናገርሽ!" አሏትና፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ተጠቃልሎ የተገለጠባቸውንና የታወቀባቸውን፥ አራቱን መሠረታውያን ጸሎቶች የያዘውን ሕያው መዝገብ፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ ከግእዝ ወደኢትዮጵያኛ የተመለሰውን ትርጉም፡ አንድ በአንድ እያነበቡ፡ በዝርዝር አስሰሟት፡-

## የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት የሃይማኖት ጸሎት።

እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡-

ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የአብ ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ በእርሱ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን፡ የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ ሥጋ፥ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡ ፍጹም ሰውን ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱም ቀኝ፡ በዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከአብ የሠረፀና በነቢያት አድሮ የተናገረው፥ በሓዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሓዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።

ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

በሙታን ትንሣኤ፥ በሚመጣውም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፥ አሜን።

## የኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የቃል ኪዳን ጸሎት።

እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡-

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች፡ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን።

አምላካችን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ **በመጀመሪያው የአበው ዘመን፡** በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ **በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤** ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቁርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤ **በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡** በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፥ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሓድ፡ በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤ **በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡** ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው።

ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀደመው ዘመን፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን።

እርሷ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን "ኢትዮጵያውያን" ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕያዋን እናትና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን።

አረንጓዴ ብጫ ቀይ የኾነው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለው፡ መለኮታዊ ቃልና ለድንግል ማርያም የተነገረው፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን።

በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር በመንፈስ፡ የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን።

ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢአታችንን ዘወትር፡ በንስሓ እያጠራንና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበልን መኖር እንዳለብን እናምናለን።

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ፍቅር ኾነን፥ በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

## ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት፡ የምስጋና ጸሎት።

አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! **“እናንተ ስትጸልዩ፡ 'የሰማዩ አባታችን ሆይ! ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ! ፈቃድህ በሰማይ እንደኾነች፡ እንዲሁ በምድርም ትኹን! የየዕለቱን ምግባችንን፡ ስጠን ለዛሬ፤ ኃጢአታችንንና በደላችንን፡ ይቅር በለን፥ እኛም የበደሉንን፡ ይቅር እንደምንል! አቤቱ፡ ወደፈተና አታግባን! ከክፉው ኹሉ፡ አድነን እንጂ! ይህች መንግሥት፡ የአንተ ናትና፥ ኃይልና ምስጋናም፤ ለዘለዓለሙ!' በሉ!”** ብሎ፡ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትክልን።

ምሕረትህን አደረግህልን። ፍቅርህን ፈጸምክልን። ጸጋህንም ሰጠኸን። ስለዚህ እናመሰግንሃለን።

ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን። ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ በምድርም የምትኖር ኾንህ። ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ። መንግሥትህም መጣችልን። በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም እንዲሁ ኾነ።

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን። ለዘላለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንን፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን። በእርሱም፡ ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን። እኛም የበደሉንን ኹሉ፡ እንዲሁ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

የአንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን።

ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፥ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን።

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን።

**“ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ”** በተባለው፡ በንጉሣችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፥ ኃጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን።

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም፡ ያንተ ናቸው፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

# ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት፡ የሰላምታ ጸሎት፡፡

እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ “ሰላም!” እንልሻለን፡፡ በአሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ፡፡ በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡

ማሕፀንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ፡፡ ቀድሞ በነቢያት፡ “ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር” የተባልሽ፥ እኛም፡ “እምነ ጽዮን!” ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር፡ ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ፡፡

እግዚአብሔር አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳነ ምሕረቱን ለዘለዓለም ፈጽሚልና፡ “ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ!” እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን፡፡

በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንቺ፡ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥ እኛም ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ፡ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም እንደማይለየን እናምናለን፡፡ ይህን ያደረገ፡ ቸሩ አባታችን፡ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፡፡ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

ኢትዮጵያዊው የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡ ንባባቸውን እንደጨረሱ፡ "ታዲያስ! ሃይማኖትሽ ይህ ነውን?" ሲሉ፡ ሕመምተኛዋን ጠየቋት።

እርሷም፡ "አዎን! ይኸው ነው!" አለች፡ በማስረገጥና በሚያስተማምን ቃል። መልሷንም በመቀጠል፡ "እኔኮ፡ ከቀደሙት መጽሐፎችዎ መካከል፡ ያነበብኋቸው አሉ፤ በእነዚህም መጻሕፍት ውስጥ፡ አንዳንዶቹ፡ እነዚህን፡ አኹን፡ በንባብ ያስሰሙኝን ጸሎቶች ይዘው አግኝቻቸው፡ እምነቴን አስተካክዬና አጣርቼ አጽንቼባቸዋለሁ።" አለቻቸው።

በዚህ ጊዜ ካህኑ፡ በረካና በፈካ ስሜት፡ "ኣሃ! ለካ ይህ እምነትሽ ነው፡ በፈተናሽ እንድትጠናከሪ፥ ወደእኔም እንደትደውዪ ያደረገሽ!? እንግዲያማ፡ ለመዳንሽ፡ ምንም ጥርጥር አይኖርም!" የሚለውን የአንክሮ ቃል፡ በመገረምና አንደበታቸውን ከፍ በማድረግ ተናገሩ። አከታትለውም፡ "ከዚሁ ከምንነጋገርበት ጉዳይ ጋር የተያያዘ፡ ሌላ ቍም ነገር ስላለ፡ እዚህ ላይ፡ ያንን አስቀድሜ ላነሣብሽ እፈልጋለሁና፡ ታዳምጪኝ ዘንድ፡ ዓቅሙና ጊዜው ይኖርሻል?" የሚል ጥያቄን አቀረቡላት።

"እንኳን አገኘሁዎት እንጂ፡ በእርስዎ በኩል 'በቃ!' እስኪሉኝ ድረስ፡ በእኔ በኩል፡ በንግግራችን እንድንቀጥል ነው የምፈልገው።" አለቻቸው።

"እንግዲያው፡ ላነሣብሽ የፈለግሁት ቍም ነገር፡ የሕመምሽ ባሕርይ ምን ዓይነት እንደኾነ ለማወቅ፡ አንቺም፥ እኔም፡ ተገቢውን ጥረት ልናደርግ የሚገባን መኾኑን የሚያመላክተው እውነታ ነው።

"ስለዚህ፡ ሕመምሽ፡ በእርግጥ የርኩስ መንፈስ ልክፍት ነው? ወይስ፡ የራስሽ የአእምሮ ጭንቀት ያስከተለው የነፍስ መታወክ ነው? የሕመምሽ መንሥኤ፡ ከእነዚህ ኹለት የተለያዩ ምንጮች ውጭ ሊኾን አይችልምና፡ 'የሕመምሽ ምንጭ፡ የትኛው እንደኾነ ለይተን ለማወቅ ጥረት ማድረግ አለብን!' ያሰኘው፡ ምክንያቱ ይህ ነው።

"እንግዴህ፡ የሕመምሽ ምንጭ፡ ከእነዚህ ጠንቆች አንዱ መኾኑ ከታወቀ፥ ወይም፡ ኹለቱም የሕመም ዓይነቶች በአንድነት የሚያሠቃዩሽ ቢኾንም እንኳ፡ አኹን ባለሽ የእምነት ጽናትና የምግባር ቆራጥነት፡ ለአንዱ ኾነ ለኹለቱም ሕመምሽ፡ ፍቱን የኾነውን መድኃኒት አግኝተሽ፡ ፈውስሽን ልትቀዳጂ፡ ቀላልና አመቺ ይኾንልሻል፤ በፍጹም መዳኑ ይቻልሻል ማለት ነው።

"እንዲያውም፡ ሕመምሽ፡ የርኩስ መንፈስ ልክፍት፥ ወይም ቍራኛ ከኾነ፡ ከእምነትሽ እውነተኛነትና ከምግባርሽ ቀናነት የተነሣ፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ በቀላሉ ሊወገድልሽና ጤናሽ ሊመለስ ይቻላል። በአእምሮ ጭንቀት፥ ወይም፡ በልዩ ልዩ ሱስ ከመጠመድ የተነሣ፡ በራስሽ ላይ ራስሽ ያመጣሽው ጠንቅ ከኾነ ግን፡ በራስሽ ቆራጥነት ብቻ የሚወገድ ይኾናል። ታዲያ! ይህን እውነታ አውቀሽውና አምነሽበት፡ ልትፈጽሚው ይቻልሻል?" ሲሉ፡ ኢትዮጵያዊው አገልጋይ ጠየቋት።

እርሷም፡ "አዎን! አውቄዋለሁ፤ አምንበታለሁ፤ እፈጽመዋለሁም!" አለች፡ በአጽንዖት ድምፅ።

"እንግዲያውስ፡ ‹እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል!› የሚለው፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ቃል፡ 'እናንተ፡ በፍጹም እውነተኛ እምነት ኾናችሁ፡ የአምልኮ ጸሎታችሁን ካቀረባችሁልኝ፡ እኔ ደግሞ፡ በመንፈስ፡ ለዚያ ጸሎታችሁ፡ የሚያስፈልጋችሁን መልካም ምላሽ እሰጣችኋለሁ!' ማለት ነውና፡ ለእኔ፡ ቀደም ብለሽ፡ በቃልሽ ባረጋገጥሽልኝ እምነትሽ ኾነሽ፡ ይህን የመሰለውን ማረጋገጫ ቃሉን ላስሰማን፡ ለታመነው፡ ቸሩ ፈጣሪያችን፡ የምስጋናና የልመና ጸሎትሽን፡ አኹኑኑ አቅርቢለት፤ ፈውሱን፡ ወዲያው ታገኚያለሽ።" አሏት፡ ካህኑ።

ሕመምተኛዋም፡ ለመዳን በመጓጓት፡ "እኔ፡ አኹን፡ ምን ብዬ እንደምጸልይ አላውቅምና፥ እንግዴህ፡ እርስዎም፡ ሊመጡልኝ የማይቻልዎ ከኾነ፡ በዚሁ፡ በስልኩ፡ እርስዎ፡ ጸሎቱን እየነገሩኝ፡ እንድጸልይ ያድርጉኝ!" ብላ ካህኑን ተማጸነች።

እርሳቸውም፡ "እሺ! መልካም!" አሏት፤ ወዲያውም፡ ነገራቸውን ቀጠል አድርገው፡ "ነገር ግን እኮ፡ አንቺም፥ እኔም፡ የምንጸልየው፡ ሌላ፡ የተለየ ጸሎት የለንም፤ ጸሎታችንማ፡ እነዚያኑ፡ አራቱን፡ የሃይማኖት፥ የቃል ኪዳን፥ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎታቱን የያዘው፡ ሕያዉ መዝገበ ጸሎታችን ነው!" ብለው፡ ጸሎታቱን፡ በኢትዮጵያኛው ቋንቋ (በዐማርኛ)፡ ቃል በቃል፡ ለሕመምተኛዋ እየተናገሩ፡ ማስደገም ጀመሩ።

ኢትዮጵያዊው አገልጋይ፡ እነዚህን ጸሎቶች፡ ከልጅቷ ጋር፡ በቃለ ምልልስ መልክ በሚያደርጉት ምንባብ፡ እያስደገሚት ሣሉ፡ የሃይማኖቱን ጸሎት ጨርሰው፡ የቃል ኪዳኑን ጸሎት፡ ገና በማካኼድ ላይ እያሉ፡ ድንገት፡ ልጅቷ፡ በስልኩ ውስጥ፡ የእርሷን ያልመሰለ፡ ኃይለኛ ጬኸትን አሰሰማች። በተለየ ድምፅና ቃልም መናገር ጀመረች።

በዚህ ጊዜ፡ በእርሷ ዘንድ፡ በዚያ መኖሪያ ቤት ውስጥ ያሉት ሰዎች ኹሉ ተደናግጠው ሲራወጡ፡ ካህኑ ግን፡ ምክንያቱን አውቀውት ኖሮ፡ ሳይሸበሩ፡ መልእክቱን፡ በንባብ ማስሰማታቸውን ተያያዙት፤ ከዚያ፡ ከሚያካኺዱት፡ ከጸሎታቱ ቃለ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሳዊ ኃይል የተነሣ፡ በመለኮታዊው ነደ እሳት ተቃጥሎ ኖሮ፡ በልጅቷ ሰውነት ውስጥ ተሠውሮ ያሠቃያት የነበረው፡ ያ፡ ባለብዙ ሠራዊት ጋኔን፡ በግዱ ተከሠተ!

ካህኑም፡ ንግግራቸው፡ ከዚች አፍታ ጀምሮ፡ ከልጅቱ ጋር መኾኑ ቀርቶ፡ ከርኩሱ መንፈስ ጋር ኾኖ፡ "በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፡ ፩ዱ አምላክ፤ በስማ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ፤ በኃይለ መስቀሉ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ!" በሚለው፡ የጸሎት መክፈቻና በሥልጣነ ክህነታቸው፡ "እንግዴህ ታሥረሃልና፡ መልስህን ስጥ!" ብለው ጠርቀው ይዘው፡ ግዳጃቸውን፡ በተረጋጋ መንፈስ፡ መወጣታቸውን ቀጠሉ፡- "አንተ ማነህ?"

ልጅቱን ሊያሠቃይ እየሞከረ ያለው ርኩሱ መንፈስ፡ በሕመምተኛዋ ሰውነት ውስጥ እንዳለ፡ ያ፡ "አላስቀምጥ" ብሎት፡ ሲያወራጨው ቆይቶ፡ አኹን፡ ድንገት እንደእሳተ ገሞራ የፈነዳበት፡ የእምነቷ ጽኑ ነበልባል፡ እያቃጠለ ስላስጨነቀው፡ ለካህኑ ጥያቄ፡ መልሱን በመስጠት ፈንታ፡ ያልተጠየቀውን፡ የተለያየ ታላላቅ ነገሮችን በማንሣት፡ የቆጥ የባጡን ይቀባጥር ጀመር።

ብዙ ሠራዊቱን ይዞ የሠፈረባት መኾኑን ከመግለጽ በቀር፡ ስሙን መንገር ያልፈለገው፡ ይኸው ጋኔን፡ በሥቃይ የተጐሣቈለውንና በጾም የተዳከመውን፡ የልጅቱን ሰውነት፡ በበለጠ እያዛለ፡ ትንፋሿን ሊያስቆርጥ መጣሩን፡ ሥራዬ ብሎ እንደያዘው፡ ካህኑ፡ በረቂቁ መንፈሳዊ እውቀት ስለደረሱበት፡ "እንግዴህ፡ መቀባጠርህ ይበቃልና፡ በቅድስት ሥላሴው እግዚአብሔር፥ በኢየሱስ ክርስቶስና በእናቱ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም፥ በመስቀሉም ኃይል፡ እኅተ ሚካኤልን ፈጽመህ ለቅቀህ፡ ከመላ ሰውነቷ ውጣ!" ብለው አዘዙት።

የአጋንንቱ አለቃ ግን፡ እየተንቀጠቀጠ፡ የምነግርህ፥ እንድነግርህም የተገደድሁበት አያሌ ነገር አለኝና፥ ያንንም፡ ለአንተ ሳልናዘዝ አልኼድምና፡ ይህችው፡ ስታስቸግረኝ የኖረችው፡ መንቻካ ልጅ አለችበት፡ እዚሁ፡ ድረስ ናና እለቃለሁ እንጂ፡ ከሕፃንነቷ ጀምሬ አፍቅሬና ይዤ፡ ሳልታወቅ፡ በውስጧ ተሠውሬ፡ ለረዥም ዘመን ዐብሬያት የኖርኋትን ወዳጄን፡ እንዴት፡ አኹን፡ እንዲህ ባጭር ጊዜ ውስጥ፡ በቀላሉ እለቃታለሁ? አልለቅቅም!" ብሎ ድርቅ አለ።

በዚህ ጊዜ፡ ዋጋ የሌለውና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ በቅጽበት ሊወገድ የሚችለው፡ ይህ፡ የርኩሱ መንፈስ ድርቅና ሳይኾን፡ ከግማሽ መዓልትና ሌሊት በላይ፡ ሳይቋረጥ በተካኼደው የቃላት ልውውጥና የንግግር ውዝግብ ምክንያት፡ ፈጽማ የተዝለፈለፈችውን ልጅ፡ ከባሰ ውድቀትና አሳዛኝ ፍጻሜ ለማዳን ሲሉ፥ መንፈስ ቅዱስም፡ "ይህ እንዲኾን የፈቀደበት፡ ልዩ ምክንያት ኖሮት ይኾናል!" ብለው በማመን፡ ካህኑ፡ ለጋኔኑ፡ ከማሠሪያውና ከማስጠንቀቂያው ቃል ጋር፡ እንዲህ የሚለውን ትእዛዝ ሰጡት፡-

"ደግ ይኹን! ራሴ፡ በአካለ ሥጋ፡ እዚያው፡ አንተ አድረህበት የምትገኝበት የእኅተ ሚካኤል የተቀደሰ ሰውነት አለበት ድረስ እመጣለሁ፤ እስከዚያው ጊዜ ግን፡ እኔ መጥቼ፡ ከእሥራትህ እስክፈታህ ድረስ፡ በዚህች ልጅ ኹለንተና ሰውነት ላይ፡ አንዳች ጉዳት እንዳታደርስ፥ በእግዚአብሔር አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፥ አምላክን በወለደች፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ስምና የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው፡ በ፩ቱ ማዕዝናተ ዓለም ተቸንክሮ በተፈተተበትና ክቡር ደሙ በፈሰሰበት በመስቀሉ ኃይል፥ ስመ ጥምቀቷ በኾነው፡ በሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ሠይፍ፥ የእግዚአብሔርዋ መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ በኾንሁት፡ በእኔም፡ በኢትዮጵያዊው ሥልጣን አሥሬሃለሁ!"

ይህንም ብለው፥ ወደልቧ ለተመለሰችውና ለተዳከመችው ልጅም፡ "አይዞሽ! እንደፈለግሽውና እንደጠየቅሽኝ፡ በነገው ማለዳ ተነሥቼ እደርስልሻለሁ፤ እስከዚያው፡ በሥጋሽም፥ በነፍስሽም፥ በመንፈስሽም ተጠናከሪ! ለቤተሰቦችሽም፡ እንድትበረቺ፡ ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያደርጉልሽ እነግራቸዋለሁና፡ በዚህ ረገድ የሚሉሽን ኹሉ፡ 'እሺ!' ብለሽ ተቀበዪ!" ካሉ በኋላ፡ ቤተሰቦቿም፡ ይህንኑ፡ እንዲፈጽሙ፡ እነርሱን፡ "አደራ!" ብለው፡ በጊዜያዊ የስንብት ቃል፡ ስልኩን ዘጉት።

ኢትዮጵያዊው አገልጋይ፡ በማግሥቱ፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ በአንድ የአየር መንገድ ጥያራ፡ መቀመጫ ቦታ አግኝተው፡ ከባለቤታቸውና ከአንዱ ልጃቸው ጋር ኾነው፡ በማለዳ፡ ከዋሽንግተን ዲ.ሲ. ከተማ ተነሥተው፡ ማምሻውን፡ ከሎስ አንጅለስ ከተማ ደረሱ። ሕመምተኛዋ ካለችበት መኖሪያ ቤት ሲገቡ፡ በሰላማዊ ዕረፍት ላይ የቆየችው ወጣት፡ ገና ስታያቸው፡ ያደረባት ርኩስ መንፈስ ተቀስቅሶባት፡ በአንደበቷ እየጮኸ፡ የተለመደ ድንፋታውንና ቅብጥርጥሩን፡ እንዲህ በሚል መክፈቻ ማሰማት ጀመረ።

"አንተ ሰው! በደኅና ገብተህ፡ ልታስጨንቀን እንግዴህ መጣህብን? እኔኮ፡ 'ካልመጣህ አልለቃትም!' ያልሁህ፡ መቼም፡ በዚህ አገር፡ ኃይላችንና ሥልጣናችን፡ የተንሰራፋ ስለኾነ፡ ወደዚህ ለመድረስ የምትጓጓዝበትን፡ የየብስ ኾነ፥ የአየር፥ ወይም የባሕር መመላለሻ፡ አደጋ ላይ እንዲወድቅ በማድረግ፡ አንተንም፡ በዚያው ጉዞህ ላይ "አጥፍተን እናስቀርሃለን!" ብለን ወስነን ነበር።

"አንተ ግን፡ መች የምትቻል ነህና! በአገርህ ስታስጨንቀንና ስታሳድደን የቆየኸው አንሦ፡ አኹን ደግሞ፡ እዚህ፡ እሠለጠንበትና ግዛታችን በኾነው አገር ድረስ መጥተህ ታሠቃየናለህን?" እያለ ዋይታውን እያወረደው ሣለ፡ ካህኑ፡ አጭር ጸሎታቸውን ጨርሰው፡ ንግግሩንና ዋይታውን እንዲያቆም፡ በፈጣሪና በእናቱ ስም፥ በመስቀለ ኢየሱስም ኃይል ከገሠፁት በኋላ፡ ያደረባትን ልጅ ሰውነት ለቅቆ እንዲወጣ፡ በኢትዮጵያዊው የቅዱሱ ኪዳን ክህነታዊ ሥልጣናቸው ወጥረው ይዘው አስጨነቁት።

የጾም፥ የጸሎትና የምጽዋት ምግባራት የተጠመዱበትን፡ የኹለት ሱባኤን (ኹለት ሳምንታትን) ዕድሜ የወሰደውን፡ ረዥሙንና የከበደውን መንፈሳዊ ሰልፍና ተጋድሎ፡ እንዲህ በሚል፡ አጭር ቃል ማጠቃለል ግድ ይኾናል።

ሠራዊቱ ብዙ የኾነው፡ ይኸው ርኩስ መንፈስ፡ በልጅቷ ሕይወት፡ ከሕፃንነቷ አንሥቶ፡ እስከአኹን ዕድሜዋ ድረስ ሲያካኺድ የኖረውን የክፋትና የጥፋት ድርጊት እየዘከዘከ ከመናገሩ በላይ፡ ለመዘርዘር የሚያሰለች፡ እጅግ የበረከተ፡ የዘመኑን ግለሰባዊና ቤተሰባዊ፥ ማኅበራዊና ኅብረተሰብአዊ፥ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ጉዳዮችን ሳይቀር የሚያጣቅስ፡ ከፍተኛ ጉዳዮችን እያነሣ መናገሩን፡ የማያቋርጥ ኾነ።

በካህኑ በኩል፡ "ይህ ኹሉ የማይፈለግ ዝባዝንኬ ስለኾነ፡ ይህን ትተህ፡ ልጅቱን ብቻ ለቅቀህ ውጣ!" እያሉ፡ ደጋግመውና መላልሰው፡ በአጽንዖትና በግሣጼ ከመወትወት አላረፉም።

የአጋንንቱ አለቃ ግን፡ "የለም! ልገልጥልህ የሚገባኝና ሳልነግርህ የማላልፈው ነውና፡ ይልቅስ፡ በጥሞና ስማኝ!" እያለ፡ ውዝግቡን፡ ለኹለት ሳምንታት ያህል ከመቀጠል በቀር፡ ወደኋላ ሊል ከቶ አልቻለም።

በመጨረሻ ግን፡ ቊጥሩ እጅግ የበረከተ ጭፍራ ያለው ይኸው ጋኔን፡ "ታዲያ! ወዴት ነው ኺድ የምትለኝ?" በሚል ጥያቄና በጽኑ ለቅሶ፡ ከልጅቷ ወጥቶና ተሰናብቶ እንዲኼድ፥ ኹለተኛም፡ ወደእርሷ ተመልሶ ላይጎበኛት፥ በሌላ ፍጡርም ላይ እንዳይሠፍር፡ በፈጣሪና በአምላክ እናት፥ በቅዱሳንም ስም ምሎና ተገዝቶ እንዲለቅቃት ተደርጓል።

ልጅቷም፡ የተፈለገውን ፈውስ አግኝታ፡ በጤና፣ በደኅና፡ ወደአገርዋና ወደወላጆቿ ለመመለስ በቅታለች። ለእግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ እና ለአምላክ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ምስጋና ይድረሳቸውና!!!

ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቷ፡ ራሷን ያበቃችው፡ እኅተ-ሚካኤል፡ ጤናዋ ተስተካክሎ፡ በደኅና፡ ወደአገርዋና የልደት ሰበካዋ በመመለሷ፥ በወላጆቿና በቤተሰቧም መካከል እንደገና በመገኘትዋ፥ በዚህ ጠንቀኛ ሕመም ምክንያት፡ "ልጃችንን ልናጣ ይኾን?" ብለው፡ በጭንቀትና በምጥ ተይዘው፡ ሲናውዙ የቆዩት ወላጆቿም፡ ልጃቸውን፡ ባልጠበቁት በመልካሙ መልክና ይዘት፡ ወደዕቅፋቸው ተመልሳ በመግባቷ፡ ኹሉም፡ እጅግ ደስ ብሏቸው፡ ለፈጣሪያቸው፡ ልዩ ምስጋናቸውን አቀረቡ፤ ስለበጎ አገልግሎታቸውም፡ ንቡረ-እድንና ባለቤታቸውን፥ ተባባሪዎች ልጆቻቸውን ጨምረው መረቁ።

፪ኛ. እኹሁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው የኢትዮጵያ አገልጋይ፡ ወደዚችው የተፈወሰች ዕድለኛ ልጅ ዘንድ ኼደው በሰነበቱባቸው በእነዚሁ፡ ኹለት ሳምንታት ውስጥ የኾነውን፡ የምሥራች ዝክረ ነገር ደግሞ እናውጋችሁ!

አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት፡ በቅርቡ፡ ወደአሜሪካ መጥቶ በመኖር ላይ ሳለ፡ ብርቱ የኾነ የመንፈስ መታወክ ሕመም ያድርበታል፤ ይህም ሕመም፡ ድንገት፡ ራሱን እየሳተና እየወደቀ፥ እየተወራጨና እየለፈለፈ በሚያሳየው፡ ኃይለኛ የልክፍት በሽታ ኹኔታው ምክንያት፡ የርኩስ መንፈስ መጠናወትና መፃረር መኾኑ፡ ተረጋግጦ ይታወቃል።

ስለዚህ፡ በራሱ መንፈሳዊ የሃይማኖት ኃይልና በሌሎችም ግፊት፡ ኢትዮጵያውያን ካህናት ወዳሉበት ቤተ ክርስቲያን ይኼዳል፤ ይመላለሳልም። እዚያም፡ በሥርዓተ ጸሎቶቹ ላይ እያለ፡ ሕመሙ እየተነሣበት ሲሠቃይ፡ ምእመናኑም፥ ካህናቱም፡ እየተመለከቱ፡ እንደተገቢው ሥርዓት፡ በጸሎትና በጥምቀት፤ በቅዱስ ቅብዓትና በመስቀል ክህነታዊ ኃይል፡ ይህንኑ፡ በርኩስ መንፈስ የሚሠቃየውን ወጣት በመርዳት ፈንታ፡ ሕመምተኛው፡ ማድረግ የማይፈልገውን፡ ዘመናዊው የሕክምና እርዳታ ወደሚሰጥበት ቤተ ሕሙማን፡ ያለፈቃዱ፡ እንዲኼድ፡ በሕግ ዘቦች ሳይቀር ይገደዳል።

ይህን አሳዛኝ ኹኔታ የተመለከቱና በበኩላቸው ተገቢውን እርዳታ ያበረከቱለት፡ ኹለት ባልና ሚስት ወጣቶች፡ እነርሱ ሕይወት አድርገው በሚኖሩበት፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸው ኃይል፡ በለባስያነ ሥጋና በመንፈሳውያን ርኩሳን አጋንንት ላይ እየተካኼደ ያለውን፡ የመንፈስ ቅዱስ ትንግርታዊ የማሳደድ ትድግና ስለሚያውቁ፡ ለእኹሁ ለኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡ ለንቡረ-እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ ስልክ ይደውላሉ፦

"ሀለውኩ! አቤት!" የሚል ድምፅ፡ ከስልኩ ተቀባይ ይሰማሉ።

"እባክዎ! ንቡረ እድን እንፈልግ ነበር?!"

"የሉም፡ ወደሌላ ግዛት ኼደዋል። ሲመለሱ፥ ወይም፡ ስልክ የደወሉ እንደኾነ፡ እንነጋራቸው ዘንድ፡ እርስዎን ማን ልበል? መልእክት ካለዎም፡ እናደርሳለን።"

"ለነገሩ፡ ጉዳዩ አስቸኳይ ነው! እዚህ፡ እኛ ዘንድ፡ በርኩስ መንፈስ የሚሠቃይ፡ አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት ስላለ፡ ስለእርሱ ልናዋያቸው ነበር የፈለግናቸው።"

"ታዲያ! ምን ችግር አለ? የስልክ ቍጥራችሁን ስጡኝና፡ እርሳቸው፡ ወደእናንተ ቀጥታ ደውለው ያነጋግሩዋችኋል።" በማለት፡ የስልክ መላሹ፡ መልእክቱንና የደዋዮቹን ስልክ ቁጥር ይጽፉል፤ ከደዋዮቹም ተሰነባብቶ፡ መነጋገሪያውን፡ በማረፊያው ላይ በማስቀመጥ ይዘጋዋል።

ወዲያው፡ ብዙም፡ ሳይቆይ፡ ስልኩ እንደገና ይደውላል።

"አለሁ!" ይላል፡ ስልክ ተቀባዩ።

"እንዴት ናችሁ? ዛሬ ማምሻውን እንገባለንና፡ እንድትቀበሉን!" ብለው ከንቡረ-እድ ጋር ተጉዘው፡ በዚያ አገልግሎት ሳይለይዋቸው፡ ዐብረዋቸው የሰነበቱት፡ ባለቤታቸው፡ ኪዳናዊት እመቤት ራሔል ዘካርያስ፡ በሚነሡበት አየር ማረፊያ ኾነው ይናገራሉ።

ስልክ ተቀባዩ፡ በአጋጣሚው፡ እጅግ ተገርሞ፡ "እሺ እቴትዬ! ደኅና ግቡልን!" አለ፡ መናገሪያውን፡ ወደቦታው እየመለሰና፡ የተቀበላቸውን፡ አንዳንድ መልእክቶች፡ "ያው ሲገቡ መንገሩ ይሻላል!" እያለ በማሰብ።

መንገደኞቹ፡ እቤት እንደገቡ እና ያ፡ ስለሕመምተኛው ወጣት የሚጠብቃቸው መልእክቱ እንደደረሳቸው፡ ንቡረ-እድ ይደውሉና፡ ደዋዮቹን ያነጋግራሉ።

እኒያ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕይወት የሚኖሩት እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ባልና ሚስት፡ በሕመምተኛው ኢትዮጵያዊ ወጣት ላይ ስለደረሰው ኹኔታ፥ በቤተ ክርስቲያንም በኩል፡ ፈውስን ቀርቶ፥ ተቀባይነትንና ትብብርን፡ በምንም ዓይነት ሊያገኝ ያለመቻሉን ነገር፡ ከመነሻው እስከመድረሻው፥ በየበኩላቸውም፡ ሲያደርጉ የቆዩበትን፡ የእርዳታ ዓይነት፡ ለንቡረ-እድ፡ በዝርዝር አስረዷቸው።

እርሳቸውም፡ ከዚህ የሚከተለውን መልስ ሰጧቸው:-

"አስፈላጊ ከኾነ፡ እኔ፡ አኹኑኑ፡ በጥያራ ተነሥቼ መምጣት እችላለሁ። ዳሩ ግን፡ የእኔ፡ ወደዚያ፡ ወደእናንተ መጥቼ፡ በሕመምተኛው አጠገብ፡ በአካለ-ሥጋ መገኘት፥ ወይም፡ ሕመምተኛው፡ ወደዚህ፡ ወደእኔ መጥቶ፡ በአጠገቤ መገኘት፡ አስፈላጊነቱ፡ ይህን ያህል ጠቃሚና ተገቢነት ያለው አይደለም። ይልቅስ፡ ለሕመምተኛው ፈውስና ደኅንነት፡ በእርግጥ የሚያስፈልገው፡ ይህ ሳይኾን፡ ከዚህ የበለጠውና የተሻለው ሌላው ምርጫ ነው።

"አዎን! የሚያስፈልገው፡ ይህ ሳይኾን፡ የራሱ የኢትዮጵያዊነቱ እምነት ትክክለኝነትና እውነተኛነት፥ የምግባሩም ጽናትና ቀናነት ብቻ መኾኑን፡ እናንተማ፡ በሚበቃ አውቃችሁ የምትገኙበት ሃይማኖታችሁና የምትኖሩበት ሕይወታችሁ አይደለምን? ለክህነቱም እኮ፡ ከዚሁ፡ ከቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ እምነታችሁ የተነሣ፡ በኪዳነ መልከ ጼዴቅ ምክንያት፡ ኹለታችሁም፡ ካህናት ናችሁ። እስካኹንስ፡ በእየራሳቸው፡ "ካህናት ነን!" በሌሎችም ዘንድ፡ "ካህናት ናቸው!" የተባሉት ወገኖች፡ በዚህ ሕመምተኛ ወጣት ኢትዮጵያዊ ላይ እያካኼዱ ያሉት፡ የግዴለሽነትና የቸልተኝነት፡ አሳዛኝ ድርጊት፡ ይኸው፡ በይፋ የሚታይ አይደለምን? ለዚህስ የኃላፊነት ጒድለትና ተጠያቂነት፡ ምስክሮቹ፡ እናንተ ራሳችሁ አይደላችሁምን? በዚህ አንጻር ደግሞ፡ እናንተ እያበረከታችሁለት ያለውን የአገልግሎት ምጽዋት፡ ይኸው፡ ኹሉም የሚመለከተው አይደለምን?

"ስለዚህ፡ እውነተኛነቱ፡ ይህም ማለት፡ እምነቱ፡ በእርሱ፡ በሕመምተኛው ዘንድ ካለ፥ ክህነታዊው አገልግሎት ደግሞ፡ በእናንተ በኩል ከቀረበ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በመካከላችሁ ተገኝቶ፡ ርኩሱን መንፈስ፡ በማስወገድ፡ ፍጹሙን የነፍስና የሥጋ ፈውስ፡ ለሕመምተኛው እንደሚያስገኝ፡ በቁርጥ የተረጋገጠ ነው።

"ይህን የመሰለው መልካም ውጤት ሊገኝ የሚቻለው፡

"፩ኛ፡ በመጻሕፍቴና በአገልግሎታችን የጎዋ ሰሌዳ ላይ፡ በጽሑፍ ሠፍረው በሚነበቡት፡ በአራቱ ጸሎቶች ውስጥ የተካተቱትን የእምነት ቍም-ነገሮች፡ ሕመምተኛው፡ በትክክል አውቋቸው ሲያምንባቸው ነው፤

"፪ኛ፡ ይህን እምነቱን፡ በራሱና ለራሱ ካረጋገጠ በኋላ፡ በማይታየው፡ በፈጣሪውና በቅድስት እናቱ፡ መንፈሳዊ ዙፋን ፊት፡ በዚሁ፡ በእውነተኛው የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ፡ ቆሞና ሰግዶ፡ የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ ነው፤

"ይህንኑ አካኼድ፡ ለዚሁ ሕመምተኛ፡ በግልጽ አሳውቃችሁት፡ ሥርዓቱን በሚፈጽምበት ጊዜ፡ ራሱ፡ የሚገኘው ውጤት፡ ሲመሰክር ታገኙታላችሁ።"

የቅዱስ ኪዳኗ እናት ኢትዮጵያ ታማኞች ልጆች የኾኑት፡ እኒህ ባለትዳር ወጣቶች፡ በዚሁ፡ በንቡረ-እድ መመሪያ መሠረት ለመፈጸም ተስማምተውና ቃል ገብተው፡ ተሰነባበቱ።

ንቡረ-እድ፡ "እንዴት ኾናችሁ፤" ብለው፡ የደረሱበትን ለማወቅ፡ በማግሥቱ፡ ወደእውነተኞቹ የኢትዮጵያ አገልጋዮች ሲደውሉ፡ እንዳጋጣሚ፡ ባልና ሚስቱ፡ ሕመምተኛውን ወጣት፡ ወደቤታቸው አምጥተው፡ የሚያውቁትን፡ ያን መመሪያ ተከትለው፡ በእውነተኛ ክህነታቸው፡ እያስተማሩትና እያስረዱት፥ እየገለጹለትና እያብራሩለት፥ እየመከሩትና እያጽናኑት ሣሉ ያገኟቸዋል።

የሚደውለውን ስልክ፡ ኪዳናዊው ባል አንሥቶ፡ "ሀለውነ!" አለ።

ኢትዮጵያዊው የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡ "እንዴት ናችሁ?" ብለው፡ ለሰላምታ ያህል፡ ገና መጠየቅ ሲጀምሩ፡ ለካ፡ ያች ወቅት፡ እኒሁ፡ ኹለቱ አገልጋዮች፡ "ምነው፡ በዚች ሰዓት፡ ንቡረ-እድ፡ በመካከላችን በኖሩ!" በሚል፡ የውስጥ ስሜት የተዋጡባት ጊዜ ኖራለችና፡ የስልክ ተቀባዩ፡ እኒያን፡ በአሳቡ ውስጥ የነበሩትን ሰው በማግኘቱ፡ እጅግ ደስ ብሎት፡ ገመድ-አልባ የኾነውን፡ የስልኩን መነጋገሪያ ይዞ፥ በደስታ ፈገግታም፡ ፊቱ ፈክቶ፡ ወዲያ ወዲህ ይል ጀመር።

"እንዴ! በእርግጥ፡ ንቡረ-እድ ነዎትን? እጅግ የሚደንቅ ነው፤ በኅሊናዬ ውስጥ፡ 'ምነው በኖሩ!' እያልሁ ስመኝ ነው የደወሉት፤ ሕመምተኛውን ልጅ እኮ፡ ይኸው፡ አኹን፡ እዚህ፡ እቤታችን አምጥተነው፡ እያነጋገርነው ነን፤ እንዲያውም፡ እርስዎ ራስዎም፡ በቀጥታ ድምፅዎን እንዲያስሰሙት፡ ልንደውልልዎ እያሰብን ነበርና፡ እስኪ፡ ፈቃድዎ ኾኖ ያነጋግሩት!" ብሎ፡ ከእርሳቸው፡ ምንም ዓይነት መልስ ሳያገኝ፡ በችኮላ፡ "እንካ! ንቡረ-እድን አነጋግራቸው!" እያለ ስልኩን፡ ለሕመምተኛው ወጣት ሰጠው።

ወጣቱም፡ ስልኩን ተቀብሎ፡ "ጤና ይስጥልኝ፡ አባቴ! ስለእርስዎ፡ እኒህ መካሪዎቼና አጽናኞቼ ወንድሜና እኅቴ ስለነገሩኝ፡ በዝና አውቄዎታለሁ።" አለ፡ በደከመ ድምፅና በትሕትና ቃል።

"እግዚአብሔር ይመስገን፡ እኔ ደኅና ነኝ! አንተስ፡ አኹን፡ እንደምነህ?" ብለው፡ ንቡረ-እድ ጠየቁት።

"በፈጣሪዬ ቸርነትና በእነርሱ ምክር፡ እየበረታሁ ነኝ አባቴ!" ሲል መለሰ፡ ወጣቱ ሕመምተኛ።

"ስለአንተ፡ እነኪዳነ ቃል አስረድተውኛል፤ ለመኾኑ፡ ክርስትና ስምህ ማነው?"

"ኃይለ ማርያም ነው አባቴ!"

ፈጥኖ መልስ ስለሰጣቸው፡ ኢትዮጵያዊው አገልጋይ፡ ደንቋቸውና ተደስተው፡ "ኃይለ ማርያም!" አሉት።

"አቤት! አባቴ!"

"እንግዴህ፡ አንተም፥ እኔም፥ ኹላችንም፡ የአንዱ ፈጣሪያችንና ሰማያዊ አባታችን፡ የልዑል እግዚአብሔር ልጆች ስለኾንን፡ እኔን፡ 'አባቴ!' ብለህ እንድትጠራኝ፡ አንተ ብትፈልግም እንኳ፡ እኔ አልፈቅድልህምና፡ ከአኹን በኋላ፡ አጠገብህ ያሉት ወዳጆችህ፡ ሲጠሩኝ እንደሰማሃቸው፡ ቢበዛ፡ 'ንቡረ-እድ!' አለዚያ ግን፡ 'ቄስ ኤርምያስ!'፥ ወይም፡ 'ካህኔ!'፥ ወይም፡ 'አገልጋዬ!' ብለህ መኾኑን እንዳትዘነጋ ይኹን! አደራህን! ይህን ያልሁህ፡ ለምን እንደኾነ፡ ምክንያቱን፡ ካስፈለገህ፡ ወደፊት አስረዳሃለሁ፤ በዚያን ጊዜ፡ አንተም፡ 'ትክክል ነው!' ብለህ እንደምትቀበለው አልጠራጠርም።"

"እሺ አባቴ!" አለ፡ ወጣቱ ኃይለ ማርያም። ስሕተቱን መድገሙ፡ ወዲያው ታውቆት፡ በዚያችው ቅጽበት ውስጥ፡ "ይቅርታ! እሺ! 'ንቡረ-እድ' ማለቴ ነው!" ሲል አስተካከለው።

"መልካም!" በሚል፡ ቃለ ተሰጥዎ፡ ኢትዮጵያዊው ካህን፡ ንግግራቸውን፡ እንዲህ ሲሉ ቀጠሉ፡- "በመጀመሪያ፡ ሕመምህን፡ እስካኹን፡ በአሸናፊነት ተቋቁመህ፡ ለመቆየትና ወደእኛ፡ ወደቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ምእመናን እንድትመጣ ያደረገህ፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፡ በዚሁ፡ 'ኃይለ ማርያም!' በተባልክበት፡ የክርስትና ልጅነትህ ላይ ከተመሠረተው፡ የሃይማኖትህ እውነተኛነትና ጽናት የተነሣ መኾኑን ልታውቀው ይገባሃል።

"ቀጥሎ፡ አኹንም፡ ጤንነትህን እየነሣና እንቅፋት እየኾነህ፡ ከሚያስቸግርህና ከሚያሠቃይህ፡ ከዚህ ሕመም መዳን የምትችለው፡ እውነተኛና ጽኑ በኾነው፡ በራስህ፡ እምነት መኾኑን ተገንዝበህ፡ በዚያ እምነትህ ፍናነትና መሣሪያነት፡ ውስጥህን በጥልቅ መመርመር ይኖርብሃል፤ ይህም ማለት፡ 'ሕመምህ የተነሣውና የሚስሰማህ፡ ራስህ፡ በውስጥህ፡ በፈጠርኸው፡ ከዓቅም በላይ በኾነ፡ የአእምሮ ውጥረትና የመንፈስ ጭንቀት የተነሣ መኾን ያለመኾኑን፡ በቅድሚያ፡ ፈትሸህ፡ ከእውነተኛው ውጤት መድረስ አለብህ!' ማለት ነው።

"መነሻው ምክንያት፡ ራስህ የፈጠርኸው፡ ይህ ዓይነቱ ከኾነ፡ በዚያ፡ በእውነተኛው እምነትህ ፍቱን መሣሪያነት፡ በቀላሉ፡ ፈጽመህ ልታስወግደው ይቻልሃል። ነገር ግን፡ የሕመምህ ጠንቅ፡ ርኩስ መንፈስ ከኾነ፡ ያም፡ በዚሁ ሃይማኖትህ ኃይል፡ እንዴት ሊወገድ እንደሚችል፡ እነግርሃለሁና፡ በማስተዋል፡ አዳምጠኝ!"

የሕመሙ ሰለባ የኾነው ኃይለ ማርያም፡ የንቡረ-እድን ንግግር የሚሰማውና የሚከታተለው፡ የስልኩን መናገሪያ፡ ከጆሮው አስጠግቶና አጎንብሶ፡ በተመስጦ ስለኾነ፡ የሚያዩት ይመስል፡ ከአንገቱ ቀና ብሎ፡ "እሺ!" የሚለውን መልስ ሰጣቸው።

እርሳቸውም፡ "አዎን!" ብለው፡ ንግግራቸውን ቀጠሉ፤ "አዎን! ለመዳን፡ ቍርጥ ፍላጎት ያለህ መኾንህን፥ የሚያድንህም፡ ተወልደህ ያደግህበት፡ ይህ ሃይማኖትህ መኾኑን ለማወቅህ፡ እስካኹን፡ ምንም ዓይነት እርዳታን ለማግኘት ወዳልቻልህባት ቤተ ክርስቲያንህ ባለመሰልቸት በመመላለስህ አረጋግጠሃል። ወደእኛም ያመጣህ፡ ይኸው እምነትህ መኾኑ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ እሙን ነው።

"እውነታው፡ ይህ ከኾነ ዘንድ፡ አኹን፡ ለአንተ የማቀርብልህ፡ መሠረታዊ የኾነ፡ አንድ ዋና ጥያቄ አለኝ፤ እርሱም፡ 'ታዲያ! ይኼ፡ በነፍስ፡ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርህበት፥ በሥጋ፡ ከወላጆችህ የተወለድህበትና በመንፈስ ቅዱስ፡ ከሥላሴ የተወለድህበት፡ እውነተኛው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖትህ፡ ምን እንደኾነ፡ በትክክልና በግልጽ ታውቀዋለህወይ?' የሚል ነው። ለዚህ ጥያቄዬ፡ ከኃይለ-ማርያም፡ መልስህን እፈልጋለሁና፥ እጠብቃለሁምና፡ ይህንኑ፡ አረጋግጠህ ንገረኝ!" ሲሉ፡ ወጣቱን ሕመምተኛ ጠየቁት።

ለጥቂት አፍታዎች፡ የዝምታ ቆይታ ካለፈ በኋላ፡ "በአጠቃላይ ባውቀውም፡ በዝርዝር፡ 'እንዲህ ነው!' ብዬ መናገር አልችልም።" ሲል፡ ሕመምተኛው ኃይለ-ማርያም፡ መልሱን፡ ባጭር ሰጠ።

"እየኸው እንግዴህ!" አሉት፡ ኢትዮጵያዊው፡ የቅዱሱ ኪዳን ካህን። ማብራሪያቸውንም፡ እንዲህ ሲሉ አያይዘው ቀጠሉበት፡- "ይህ አኹን፡ በመላ ሰውነትህ ውስጥ ያደረው ሕመም፡ እስከዚህና እንደዚህ ተንሰራፍቶና ሰፍኖ ሊሠለጥን የቻለው፥ በገሃድና በግዘፍም ወጥቶ እንዲህ ሊያሠቃይህ የቻለው፥ ሌሎችንም፡ በእልፍ አእላፋት የሚቆጠሩ ወገኖቻችንንና መላውን የሰውን ዘር ሊያሠቃይ የቻለው፡ ለምን መሰለህ!? <u>ከፍጹም ሃይማኖት ጕድለት የተነሣ መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።</u>

"ፍጡሩ ሰው ደግሞ፡ በፈጣሪው ላይ ያለው እምነት፡ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል ያነሰች ብትኾን እንኳ፡ ያችዋ አንዲቷ ቅንጣት፡ መቶ በመቶ ፍጹም ሙሉ መኾን እንዳለባት ኹሉ፥ አለዚያ፡ ያች፡ አንዲት ዘር፡ ጥቂት ከተፈነከተች፡ ከሙሉነቷ 'ጎደለች!' እንደምትባል ኹሉ፡ በሃይማኖትም፡ ጥቂት ጉድለት ካለ፡ ሃይማኖትነቱ ስለሚቀር፡ ለምንም አያገለግልም፤ አይጠቅምም። የሚያገለግለውና የሚጠቅመው፡ ለክፋቱ ኃይል፡ ለሰይጣን ይኾናል።

"አዎን! ይህ፡ የፍጹም ሃይማኖት ጒድለት፡ ያስከተለውን ጽኑ ጒዳት፥ አኹን፡ አንተን፡ እያሠቃየህ ያለውን ሕመም ጨምሮ፡ ለማስወገድ፡ አንድ መፍትሔ ያስፈልጋል፤ ይህም መፍትሔ፡ ከሌላው፡ ከረቀቀውና ከተወሳሰበው፥ ከከበደውና ከበዛው፥ ከሰብአዊዉና ከሰይጣናዊው የመድኃኒትና የሕክምና ዓይነት ኹሉ ይልቅ፡ እጅግ የቀረበውና የቀለለው ፍቱኑ ዓይነት፡ ፍጹሙ ሃይማኖት ኾኖ ይገኛል።

"ፍጹም ሃይማኖት ያለው ሰው፡ ከሃይማኖት ጒድለት ጠንቅ የተነሣ፡ የደረሰበትን ጒዳት፥ ወይም፡ ሕመም ለማስወገድ፡ ወደተወሰነ ቦታ ኼዶ፡ እዚያም፡ ከባለመድኃኒቱ፥ ወይም፡ ከአዋቂው ጋር ተገናኝቶና ተነጋግሮ፥ ለተለያየ ጥያቄ መልስ ሰጥቶና የተለያየ ረቂቅ የተሓዋስያን ምርመራን አድርጎ፥ ወደአፍ በሚገባ፥ ወይም፡ በሚዋጥ፥ ወይም፡ በሚሸተት፥ ወይም፡ በሰውነት አካል ላይ በሚፈስስ፥ ወይም፡ በሚቀባ የመድኃኒት፥ ወይም፡ የሕክምና፥ ወይም፡ የፈውስ ዓይነት እንዲጠቀም የሚያስገድድ ሥርዓትን የሚጠይቅ አይደለም፤ ይህን ለመሰለው ጒዳት፥ ወይም ሕመም፡ የፈውስ አማካዮች ኾነው እንዲያገለግሉ፡ በሃይማኖታውያን ተቅዋማት ዘንድ የተመደቡት፡ ቅዱስ ቅብዓት፥ በጠበልነት የሚጠጣው፥ ለጥምቀትም የሚውለው ውኃ እንኳ አያስፈልጉም።

"ይህም ማለት፡ አንተ፡ አኹን ከምትሠቃይበት ሕመምህ ለመዳን፡ ክህነታዊዉን አገልግሎት እሰጥህ ዘንድ፡ የእኔ፡ ወዳንተ መምጣት፥ ወይም፡ የአንተ፡ ወደእኔ መምጣት ሳያስፈልግ፡ የሚጓጓለት መልካሙ፡ ጣፋጭ ፍሬ፥ ይኸውም፡ የአንተ ፍጹም ፈውስ፡ በቀላሉ የሚገኝበት፡ ሌላ፡ የተሻለና የበለጠ፥ ፍቱንና ቀና  መንገድ አለ!' ማለት ነው።

"ለዚያ፡ በፍጹም ሃይማኖቱ ጒድለት ምክንያት፡ ነፍሳዊ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ጒዳት የደረሰበት፥ ወይም፡ ሕመም ያገኘው፡ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ ከዚያ ጒዳቱ፥ ወይም ሕመሙ፡ ፍጹም ፈውስን አግኝቶ ለመዳን ከፈለገ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ በውስጡ፡ ፈጣሪውን፡ በእውነትና በመንፈስ የሚያመልክ መኾኑን፡ ለራሱ አረጋግጦ፡ ይህንኑ አምልኮውን፡ በተግባር ለመግለጥ የቻለ መኾን ይኖርበታል፤ 'እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል!' የሚለውን መለኮታዊ ቃል መሠረት ያደረገና የተከተለ ሃይማኖትና ምግባር 'ሊኖረው ይገባል!' ማለት ነው። (ዮሓ. ፬፥ ፳፬።)

"አዳምና ሔዋን ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ያለውንና ዛሬ፡ የ፯ሺ፭፻፪ (የሰባት ሺህ አምስት መቶ ኹለት) ዓመታትን ያስቈጠረውን፡ የህልውናና የነጻነት ዕድሜያችንን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ያሳወቅነው፡ እኛ፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች፡ በቀጥታ፡ ከፈጣሪያችን ያገኘነውና ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈልን፡ ተረክበነውና ጠብቀነው የኖርነው፡ ሃይማኖታችንና ምግባራችን፡ ምን ዓይነት እንደኾነ፡ ልዑል እግዚአብሔር፡ በየልቦናችን ያሳደረውንና በልባችን የጻፈውን፥ እኛም፡ በጽሒፈት ቀርጸን የምናስነብበውን፥ ኹሉንም፡ አጠገብህ ካሉት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የኢትዮጵያ ልጆች ታገኘዋለህ።

"እርሱም፡ "የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የሃይማኖት ጸሎትና የቃል ኪዳን ጸሎት፥ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የምስጋና ጸሎትና ለአምላክ እናት፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም የሚያቀርቡት የሰላምታ ጸሎት" በተባሉት አራት ጸሎታት ውስጥ ተጠቃልሎ የተገለጸው ነው።

"እንግዴህ፡ አንተም፡ እነዚህን አራት ጸሎቶች፡ በሥጋዊ ዓይንህና አእምሮህ፥ ኅሊናህና አንደበትህ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በነፍሳውያኑና በመንፈሳውያኑ ጭምር፡ ከላይ እንደጠቀስሁልህ፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ኾነህ፥ በቤትህ ቆመህ፥ ወይም፡ ሰግደህ፥ ተቀምጠህ፥ ወይም፡ ተኝተህ ከተመለከትሃቸውና ከተረዳሃቸው፥ ካስተዋልሃቸውና ከተናገርሃቸው፡ በዚህ ጊዜ፡ የሚኾነውን ትንግርታዊ እውነታ፡ አስቀድሜ ላስታውቅህ ትወድዳለህ? ኃይለ-ማርያም!" ብለው፡ ማብራሪያቸውን፡ በጥያቄ ገታ አደረጉት።

የማብራሪያ ንግግራቸውን፡ በከፍተኛ ንቃት የሚከታተለው ወጣቱ ሕመምተኛ፡ ምንም ዓይነት ማመንታትንና ዝግታን ሳያሳይ፡ ፈጥኖ፡ "እንዴታ! ይህን ምሥራች ለመስማት፡ በእርግጥ እንደምፈልግ፡ እርስዎም እንደሚያውቁት አልጠራጠርም።" የሚል መልስን ሰጣቸው።

በዚህ ጊዜ፡ እርሳቸው፡ የእርሱን መተማመኛ ለማግኘት ያህል ላቀረቡት ጥያቄ፡ የጠበቁትን መልስ ካገኙ በኋላ፡ "እንግዲያ፡ በዚያን ጊዜ የሚኾነው፡ ትንግርታዊ እውነታ፡ በመላ ሰውነትህ ውስጥ በሥውር አድሮ የሚያሠቃይህ ረቂቅ ደዌ፥ ወይም፡ ርኩስ መንፈስ፡ እንደሰም ቀልጦ፥ እንደጢስ ተንኖ፥ እንደትቢያ በንኖ ሲጠፋ፥ የመጥፋቱም ትንግርት፡ በሠራ አካላትህ ውስጥና ውጭ ሲካኼድና ሲሰማህ የማግኘትህ እውነታ ነው።" ብለው፡ በማስረገጥ ነገሩት።

በሕመሙ እየቈዘመ ያለው ወጣት፡ ልዩ የንቃት ስሜት እየታየበት፡ "እርስዎ የሰጡኝን መመሪያ በመከተል፡ በመከሩኝና ባሳሰቡኝ መሠረት ለመፈጸም፡ ለእኔ፡ እጅግ ቀላል ኾኖልኛል፤ ይህን እውነታ፡ እንዲህ አብራርተው ስለገለጹልኝ፡ ከልቤ አመሰግንዎታለሁ፤ እንደእርስዎ ቃል፡ ከዚህ በሽታዬ፡ እንደምድንም አምናለሁ፤ ነገር ግን፡ ባልድንም እንኳ፡ እንደዳንሁ እቈጥረዋለሁ። ስለዚህ፡ ለሰጡኝ፡ ትምህርትና ምክርዎ፡ እግዚአብሔር፡ ወሮታዎን ይክፈል!" በማለት፡ በቅድሚያ፡ ስለተደረገለት የምክር አስተዋጽኦ፡ ባለውለተኛነቱን ገለጸ።

ከዚህ በማስከተል፡ ሊናገር ያቀደውን ነገር ሳይጀምር፡ ንቡረ-እድ አቋረጡትና፡ እንዲህ አሉት፡- "ምስጋና የሚገባው፡ ልዑል እግዚአብሔር ብቻ መኾኑን አትዘንጋ! አዎን! አንተን፡ በመልኩ ፈጥሮና በጸጋው፡ አምልቶ፡ አንተ፡ ከፈለግህና ከመረጥህ፥ ከወሰንህና ካመንህም፡ እንደእርሱ ለማሰብና ለመናገር፥ ለማድረግም እንድትችል ኃይሉን በመስጠቱ፥ አኹንም፡ ይህንኑ ፍላጎትህንና ምርጫህን፥ ውሳኔህንና እምነትህን፡ ከግብ ለማድረስ ይቻልህ ዘንድ፡ በቅዱስ መንፈሱ ስለረዳህ፥ ከእኔም ጋር እንዲህ እንድንገናኝ ስለመራህ፡ በእርግጥ ልታመሰግን የሚገባህ፡ ይህንኑ፡ ቸሩ ፈጣሪያችንን ነው።

"ለሌላው፡ ለእኔ-ብጤው ፍጡር ግን፡ 'እግዚአብሔር፡ ወሮታህን ይክፈል!' የሚለው፡ የአንተ ዓይነቱ፡ ትክክለኛ አባባል ይበቃል፤ እውነተኞቹ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ለኹሉም ዓይነት ውለታ፡ 'እግዜር ይስጥልኝ!' የሚሉት፡ በዚህ ምክንያት መኾኑን፡ የማያውቅ ያለ አይመስለኝም።"

በቍራኛ ሕመም ሲሠቃይ የቆየው ወጣት፡ በንቃቱ እየጨመረ ኼዶ፡ "በአጋጣሚው፡ ብዙ፡ ያልታሰቡ ትምህርቶችን ቀሰምሁ፤ በዚህም፡ ዕድለኛ ነኝ። አኹን፡ ወደተነሣንበት፡ ወደዋናው ፍሬ ነገር ልመልስዎትና፡ እውነተኛውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖቴን፡ በትክክልና በጥራት ለማወቅ እችል ዘንድ፡ በንባብ እንዳውቃቸው ያሳሰቡኝን፡ በጽሑፍ የሠፈሩትን አራት ጸሎቶች፡ ተመልክቼ ለመረዳት እንዳልችል የሚያግደኝ፡ አንድ ችግር ስላለ፡ ይህንኑ፡ እዚህ ላይ እገልጽልዎት ዘንድ ይፍቀዱልኝ!" አላቸው።

እርሳቸውም፡ "እሺ! ደስ ይለኛል! ግለጽልኝ!" ብለው ከመለሱለት በኋላ፡ አያይዘው፡ "አየህ ኃይለ-ማርያም! የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ ኹለንተናው፡ ከእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር የኾነ፡ የእግዚአብሔር ስለኾነ፡ በውስጡ፡ እንኳንስ፡ ለአንተ፡ ራስህን፡ 'ኢትዮጵያዊ ነኝ!' ለምትለው ወገን ይቅርና፡ ለሌላውም፡ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ ጭምር፡ "የማይገለጥ፡ የተከደነ፥ የማይታወቅም፡ የተሠወረ"፡ አንዳችም የተደበቀ ምሥጢር የሌለበት ግልጽ የኾነ ዓለምና ሕይወት ስለኾነ፡ 'ይህን ልጠይቅ! ይኼኛው ግን ይቅርብኝ!' ብለህ፡ በይሉኝታና በፍርሃት፥ በሌላም አሉታዊ አስተሳሰብ ተሰነካክለህ ልትተወው የሚገባ ክፍተት ያለበት አይደለምና፡ አይዞህ፡ የፈቀድኸውን ዘርዝረህ ተናገር!" ሲሉ፡ የማበረታቻ ቃላቸውን ለገሡት።

በካህኑ አነጋገር የተበረታታው ወጣት፡ ችግሩን መግለጽ ጀመረ፤ "'በጽሑፍ የሠፈሩትን፡ እነዚያን አራት ጸሎቶች ተመልክቼ ለመረዳት እንዳልችል የሚያግደኝ፡ አንድ ችግር አለብኝ!' ያልሁዎ፡ ወላጆቼ፡ እኔን ይዘው፡ በስደት፡ ከኢትዮጵያ የወጡት፡ እኔ፡ ገና ዐራስ ሕፃን እያለሁ ስለነበረ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ እስካኹን ድረስ፡ በቤተሰብ የተማርሁት፡ ይኸው በንግግር የማቀላጥፈውን፡ እናት ቋንቋዬን ብቻ እንጂ፡ ፊደላችንን፡ እንዳነብብ እንኳን የሚያስችል የቀለም ትምህርትን ስላላገኘሁ፡ የግእዙን፥ ወይም፡ የኢትዮጵያኛውን (የዐማርኛውን) ፊደል፡ አንዱንም እንኳ የመለየትና የመቍጠር እውቀቱ የለኝም። ስለዚህ፡ ለዋናው ችግሬ፡ መፍትሔ፥ ማለትም፡ ለፈውሴ፡ ፍቱን መድኃኒቴ የኾነውን እምነቴን አውቄ እንዳላስተካክል፡ እንቅፋት ኾኖ የተደነቀረብኝን፡ ይህን፡ የቅርብ ማሰናከያ፡ እንዴት ነው፡ እንግዴህ የማስወግደው? ምን ይመክሩኛል?" ሲልም፡ ዋይታውን፡ በእሮሮ ድምፅ አስሰማቸው።

"እንዴ! ለዚህ፡ አኹን ላለህበት ዕድሜ እስክትበቃ ድረስ፡ በዚያ፡ ይህን ለሚያህል ዘመን፡ በስደት በኖርህበት አገር፡ ታዲያ፡ ከኢትዮጵያኛው በቀር፡ በማንበብም ኾነ በመጻፍ፡ በትምህርት ቤት የተማርኸው ሌላ ቋንቋ የለምን?" ብለው ጠየቁት።

"እርሱማ አለ!"

"ምን ቋንቋ ነው፡ እርሱ?"

"እንግሊዝኛ!"

"ያ ከኾነማ፡ ኹሉ ያማረና የተስማማ መልካም ኾነልን ማለት ነው።"

"እንዴት!?" አለ፡ በድምፁ ብቻ ሳይኾን፡ በመላ ኹለንተናው፡ እየነቃ የኼደው፡ ሕመምተኛው ወጣት።

"እነዚህ፡ አኹን፡ ለአንተ የሚያስፈልጉህ አራቱም ጸሎቶች፡ ቀድሞውንም፡ የተዘጋጁት እኮ፡ በእንግሊዝኛ ጭምር ሲኾን፥ እነርሱንም፡ ታትመው ከተሠራጩት መጽሐፎቼ መካከል፡ የመጀመሪያው በኾነውና ETHIOPIA: THE CLASSIC CASE በተባለው፥ ደግሞም፡ በቅርቡ በወጣውና "ምሥራች!" በተባለው፡ በኹለቱም መጻሕፍቴ ውስጥ ታነብባቸዋለህ።" ሲሉ፡ ኢትዮጵያዊው አገልጋይ፡ ጠያቂውን ያረካ መልስን ሰጡት፤ ሊያነሣው የተዘጋጀበትን፡ ተከታይ ጥያቄውንም ሊያስቀር የቻለውን፡ የመጨረሻ ማረጋገጫ ቃልን በማያያዝ፡ እንዲህ አሉት፡- "እነዚህኑም ኹለት መጻሕፍት፡ የት እና እንዴት ልታገኛቸው እንደምትችል፡ አኹን፡ በቤታቸው የምትገኝባቸውና አጠገብህ ያሉት ኪዳናዊ እና ኪዳናዊት ወዳጆችህ፡ ማመላከት ብቻ ሳይኾን፡ ከእጅህ እንዲደርሱ በማድረግ ጭምር ይረዱሃል።"

ይህ፡ የኢትዮጵያዊው ካህን ቃል፡ ለረዥሙ የስልክ ውይይት ማብቂያ ኾኖ፡ በእውነተኛው የአምልኮ መንፈስ ላይ ከተመሠረተ ልቦና የሚመነጨውን ሃይማኖታዊ ጸሎታቸውን፡ ኹሉም፡ በያሉበት እንዲቀጥሉ ተስማምተው፡ በእግዚአብሔርና በአምላክ እናት ስም በቀረበ ምስጋናና ሰላምታ ተሰነባብተው ተለያዩ።

እኾሁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው ኢትዮጵያ አገልጋይ፡ የሕመምተኛውን የዕለት በዕለት ኹኔታ ለማወቅ፡ ከእኒያ፡ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆችና አገልጋዮች ከኾኑት ባልና ሚስት እየጠየቁና እየተከታተሉ ሣሉ፡ በመካከሉ፡ አንድ ሱባኤ (ሰባት ቀን) እንኳ ሳይሞላ፡ በተሰነባበቱ በሦስተኛው ቀን፡ ቍጥሩን የማያውቁትና ያልለመዱት የኪስ ስልክ ጥሪ ይደርሳቸዋል።

"ሀለውኩ!" በሚለው የተለመደ የአቤቱታ መልስ፡ ከፍተው ሲያዳምጡት፡ ከዚህ ቀደም የሰሙት፥ ነገር ግን ያልጠበቁት ድምፅ ይኾንባቸዋል።

እርሱም፡ "ሀለዉ! ንቡረ-እድ ነዎት?" የሚል ጥያቄ ነው።

"አዎን! ነኝ።"

"እንደምን ሰንበቱ?"

"እግዚአብሔር ይመስገን፡ እኔ ደኅና ነኝ። ማን ልበል?"

"ኃይለ-ማርያም ነኝ።"

"ላረጋግጥ ብዬ ነው እንጂ አውቄሃለሁ፤ ልትጠየቅ የሚገባህስ አንተ ነበርህ! ለመኾኑ፡ እንዴት ሰነበትህ? አኹንስ፡ እንደምን ነህ?"

"የኾነውን አስደናቂ ተአምር ልነገርዎ ብዬ ነው፡ አኹን የደወልሁልዎት።"

"ወዳጄ ሆይ! ምን ይኾን? እስኪ ልስማው!?"

"በሕመሜ ምክንያት የደረሰብኝን ችግርና ሥቃይ ለማስወገድ ሊረዱኝ፥ በቤታቸው ተቀብለው ያስተናገዱኝና ከእርስዎም ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በስልክ ተገናኝቼ፡ ያን የመሰለ ወሳኝ ውይይት ለማድረግ ያበቁኝ፡ እኒያ ወገኖቼና ወዳጆቼ፡ ከዚያ የንግግራችን መድረክ እንደተሰነባበትን፡ ወዲያው፡ በዚያችው ዕለት፡ ያን፡ ETHIOPIA: THE CLASSIC CASE የሚለውን የእንግሊዝኛ መጽሓፍዎን ሰጥተውኝ፡ ያለማቋረጥ አንብቤው ጨረስሁ።

"ንባቤን እንደጨረስሁ፡ በመጽሓፉ ውስጥ ወደሚገኙት፡ ወደአራቱ ጸሎቶች ተመልሼ፡ እርስዎ የመከሩኝን ምክርና መመሪያ በመከተል፡ ልቦናየ በሚያውቀው፥ ሕሊናዬም በሚቀበለውና ሰውነቴ በሚችለው ዓቅሜ፡ በግል ክፍሌ ተወስኜ፡ ቆሜም፥ ሰግጄም፥ ተቀምጬም፥ ተጋድሜም፡ በእውነተኛውና በመንፈሳዊው አምልኮ ኾኜ፡ እኒያን ጸሎቶች፡ ያለማቋረጥ፡ ደገምኋቸው።

"በዚህ አቋሜ ኾኜ፡ ጸሎቶቹን በምደግምበት ጊዜ ኹሉ፡ በውስጤም ኾነ በውጭ አካሌ ላይ፡ ቀስ በቀስ እየተሰማኝ የኼደው ስሜት፡ ፈጽሞ የተለየ ኾነብኝ። በቃላት ልገልጸው ግን፡ የሚቻለኝ አይደለም። ከቤተሰቤ፥ ከማውቃቸውና ከለመድኋቸው ሰዎች ጋር ስንገናኝ፡ እኔ፡ በእነርሱ ላይ ያለኝ ብቻ ሳይኾን፡ እነርሱ፡ በእኔ ላይ ያላቸው አስተያየት እንደተለወጠባቸው ጭምር፡ በግልጽ ይነግሩኝ ጀመር።

"በመጨረሻ፡ ይህን በመሰለ የረቀቀ ኹኔታ፡ በእኔ የውጭ አካሌ ላይና በውስጥ ሰውነቴ የተፈጸመውንና የደረሰውን ትንግርት፡ ቀደም ብዬ እንዳልኩዎ፡ በቃላት መግለጹ፥ ወይም ማስረዳቱ፡ ለእኔ አዳጋች ቢኾንም፥ ለእርስዎም፡ መስማቱና መረዳቱ የሚከብድዎ ቢኾንም፡ ምናልባት፡ እንዲህ በሚል አጭር ዐረፍተ-ነገር፡ ላጠቃልለው እችል እንደኾነ፡ እስኪ ልሞክር!

"ያ፡ ከራስ ፀጉሬ፡ እስከእግር ጥፍሬ ድረስ ባሉት የውስጥና የውጭ ሕዋሳቴ ውስጥ፡ ተሠግሥጎና ተንሰራፍቶ፥ አስጨንቆና ወጣጥሮ፡ የሚያሠቃየኝ፡ አንዳች የሕመም ኃይል፡ ልክ፡ የእሳት ነበልባል፡ ቅቤን፥ ወይም ሰምን፡ እያቀለጠ፡ ወደታች እንዲወርድ፥ ከዚያም፡ እየከሰመ፡ በእንፋሎትነት ተንኖ እንዲጠፋ እንደሚያደርገው ኹሉ፡ እኔም፡ በዚሁ ዓይነት፡ ከላይ፡ በጭንቅላቴ ውስጥ ከሚገኘው አንጎሌ ተነሥቶ፥ በመላው፡ የውስጥ ሕዋሳቴና የውጭ አካላቴ በኩል፡ ወደታች እያለፈና ያለማቋረጥ ቀልጦ እየወረደ መጥፋቱ፡ በውስጤ ይሰማኝ ጀመረ።

"ይህ ኹኔታ፡ ለጥቂት ሰዓቶች እየተካኼደ ከቆየ በኋላ፡ በውስጥ ሕዋሳቴም ኾነ፥ በውጭ አካላቴ፡ ፍጹም ደኅንነትና ጤንነት፥ ዕፎይታና ዕረፍት፥ ሰላምና ደስታ ተሰማኝ፤ አጥለቀለቀኝ። ይህ እንግዳ የኾነ አዲስ ስሜትና ትንግርት፡ እየኾነ ያለው፡ በእውኔ ይኹን፥ በሕልሜ፡ ለይቼ ለማወቅ፡ ሌሎች፡ ጥቂት ሰዓቶችን ፈጅቶብኛል። በእውኔ መኾኑን፡ ካረጋገጥሁ፡ ከብዙ ሰዓቶች በኋላ ነው፡ አኹን ለእርስዎ ልደውልልዎ የቻልሁት። ምን ይመስልዎታል?"

ኢትዮጵያዊው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ፡ በሰሙት፡ በዚህ ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ እጅግ በመመሰጥ፡ ለፈጣሪያቸውና ለእናቱ፡ ምስጋናቸውን፡ በጎሊናቸው እያቀረቡ፡ "ይህማ፡ 'የምሥራች!' የምንባባልበት፡ ታላቅ ዜና ነው። ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፡ ምስጋና ይኹን፡ ለቸሩ እግዚአብሔርና አምላክን ለወለደች፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም! ደግሞም፡ በይበልጥ፡ አንተን፥ ቀጥሎም፡ ኹላችንንም፡ እንኳን ደስ አለን!" በማለት፡ ሓሤታቸውን፡ ለተፈወሰው ወጣት ኢትዮጵያዊ ሃይማኖተኛ ገለጹለት።

የምክር ቃላቸውንም፡ እንዲህ ሲሉ ቀጠሉለት፡- "እንግዴህ፡ አንተም፡ ይህን ተአምራዊ ፈውስን ባስገኘልህ፡ በዚሁ ሃይማኖትህና ምግባርህ ጸንተህ መቀጠል ነው፤ እነዚህንም ጸሎቶች፡ የዘወትር ማድረግ፥ እንዲያውም፡ በቃልህ አውቀሃቸው፡ የምትጸልያቸው ሊኾኑ ይገባል።

"ፈውስህና ጤንነትህ፥ ደኅንነትህና አዲሱ ሕይወትህ፡ በቀጣይነቱ የተረጋገጠና አስተማማኝ ይኾንልህ ዘንድ፡ በመለኮቱ፡ የእግዚአብሔር አብ ልጅ፥ በሰውነቱም፡ የድንግል ማርያም ልጅ የኾነውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ምናልባት እስካኹን አልተቀበልህ እንደኾነ፡ ይህን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ማኅተም የኾነ፡ መለኮታዊ ሥርዓት፡ ያለመዘግየትና ያለማወላወል ትፈጽም ዘንድ አሳስብሃለሁ። ይህን ሥርዓት መፈጸም፡ በማቴዎስ ምሥራች፡ ምዕራፍ ፲፪÷ ቍጥር ፳፫-፳፭ ላይ ከተጻፈ የባሰ ጕዳትና ጥፋት ያድናልና።"

ተፈዋሹ ወጣትና አገልጋዩ ኢትዮጵያዊ ካህን፡ በዚህ የእርካታና የሓሤት ስሜት ከተሰነባበቱ በኋላ፡ ካህኑ፡ ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ተአምራዊ ጸጋ ምክንያት ወደኾኑት፡ ወደኹለቱ የቅዱሱ ኪዳን ባለትዳሮች ስልክ ደውለው፡ በኃይለ ማርያም ላይ የተፈጸመውን ተአምራዊ ፈውስ፡ ከአንደበታቸው አረጋገጡ። ይኸው ኹኔታ፡ ከተፈዋሹም ኾነ፡ ከእነርሱ ጋር፡ ከአንድ ዓመት በላይ ለኾነ ዘመን፡ በየጊዜው ባካኼዱት የስልክ ግንኙነት፡ እውነተኛነቱ በበለጠ እየጸና ኼዶ፥ ዛሬ፡ ለሚገኝበት ለአስተማማኙ ደረጃም በቅቶ፡ ለዚህ መልእክት መተላለፍ መንሥኤ ኾኗል።

## መፈጽም

ይህን የመሰለው ተአምራዊ ድርጊት፡ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ፡ በተለይ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ሲፈጸምና ሲታይ የኖረ ሲኾን፥ በቅርቡም፡ በተለይ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች በኵል፡ በኢትዮጵያ ውስጥም ኾነ፣ ከኢትዮጵያ ውጭ፡ በብዛት ሲካኼድ የቆየ በጎ ምግባር መኾኑን የምንገልጸው፡ በታላቅ ሃይማኖታዊ ስሜት ነው።

ስለዚህ፡ በኢትዮጵያም ኾነ ከኢትዮጵያ ውጭ፡ በመላው ዓለም ተበትናችሁ የምትገኙ የኢትዮጵያ ልጆች ኹሉ፡ ጥንታዊውና ብቸኛው፥ ትክክለኛውና እውነተኛው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ከነምግባሩና ሥርዓቱ፡ በሥጋዊውና በነፍሳዊው፥ በመንፈሳዊዉም ሕመምና ችግር ላይ፡ እየሠራ ያለውን፡ ይህን የመሰለውን የፈውስ ትንግርትና ተአምር በመመልከት፡ "እውነተኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች ነን!" የምትሉ ኹሉ፡ በዚሁ መፍትሔ እየተጠቀማችሁ፥ ማለትም፡ ይኸው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ፡ ተመሥርቶና ታንጾ የተደመደመው፡ በዚህ መልእክት ውስጥ በሠፈሩት፡ በእነዚህ፡ በአራቱ፡ የሃይማኖትና የቃል ኪዳን፥ የእግዚአብሔር ምስጋናና የድንግል ማርያም ሰላምታ ጸሎቶች ላይ መኾኑን፡ ለእየራሳችሁና ለሌሎች ወገኖች ጭምር፡ እያሳወቃችሁና እያረጋገጣችሁ፡ ከሚደርስባችሁ ረቂቅና ግዙፍ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕመም እንድትድኑ ታደርጉ ዘንድ እናሳስባችኋለን።

በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቹና አገልጋዮቹ ለኾኑት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት አማኞቹ፡ በርኩሳን መናፍስትና በክፉት ኃይላት ላይ፡ የአሸናፊነት ሥልጣንን የሰጠ ቸሩ እግዚአብሔር፡ ከቅድስት እናቱና ቅዱሳን ባለሟሎቹ ጋር የተመሰገነ ይኹን! አሜን።

\+ \+ \+